# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢ.ሕ.አ.ፓ)

## *Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)*

(አንድነት/United)


## በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ስም የሕዝብን መብት ማፈን አይቻልም!

የካቲት ፳፭ ቀን ፪ ሺህ ፲ ዓ. ም
March 4, 2018

በአንድ አገር ውስጥ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ የሚታወጀው የውጭ ወራሪ የአገርን ደህንነትና ነፃነት አደጋ ላይ ይጥላል ተብሎ ሲታመን ወይም ደግሞ የሕዝብን ኢኮኖሚያዊና ሶሻል ይዞታ ሊያናጋ የሚችል ክስተት ሲፈጠር ነው።  ክስተቱ ተፈጥሯዊ ከሆነ በሕዝብ ሕይወትና ንብረት ላይ ከፍተኛ እልቂትና ውድመትን ሊያስከትል ይችላልና ።

በአሁኑ ሰዓት በአገራችን ውስጥ ከላይ የተጠቀሱት ሁኔታዎች አልተከሰቱም። የውጭ ወራሪ ለአገሪቱ ድህንነት አላሰጋም፣ የተፈጥሮ አደጋም ይሁን በልዩ ሁኔታ ከፍተኛ ሽብርና እልቂት የሚያስከትል ሁኔታም አልደረሰም።  ያለው ዕውነታ ግፍና በደል የበዛበት ሕዝብ፣ ሕገ-መንግሥታዊ መብቱን ተጠቅሞ በሰላማዊ መንገድ ጥያቄ ማቅረቡ ነው።

ለአገራችንና ለሕዝባችን ከፍተኛ ስጋትና አደጋ የሆነው የሕዝቡ ለሰላማዊ ትግል መነሳሳት ሳይሆን፣ ህወሓት-መራሹ አገዛዝ የሚፈጽመው ሕገ-ወጥ ድርጊት ነው። አገዛዙ በፈጠረው ብልሹ አስተዳደር ምክንያት ሀገራችን እንደአገር እንዳትቀጥል ገደል አፍፍ ላይ ያደረሳት ሕዝቡ ሳይሆን፣ በሙት መንፈስ የመግዛት ቅዠት እየተገፋ ያለው የህወሓት ቡድን ነው። በመሆኑም፣ በአሁኑ ሰዓት ኢትዮጵያ ሀገራችን የሰው ልጆች መብቶች እየተረገጡ ዜጎች እየታፈኑ፣ እየታሠሩ፣ እየተገደሉ የሚኖሩባት አገር ነች።

በጎንደር፣ በኦሮሚያ፣ በባህርዳር፣ በወልድያና በሌሎችም ከተሞች በአጠቃላይ ከሰሜን እስከ ደቡብ፣ ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ በተደረጉ ሕዝባዊ ሰላማዊ ሰልፎች ላይ ሆን ብሎ በመተንኮስ ግድያ የፈጸመውና በብዙ ሺዎች የሚቆጠሩ ዜጎችን እስርቤት የከተተው ህወሓት ነው።  ህወሓት ግድያውን ከመፈጸሙ በፊት በሰልፈኛው ውስጥ አንዳችም ግጭት ሳይከሰትና ንብረትም ሳይቃጠል ፍጹም ሰላማዊ በሆነ መንገድ ነበር ብሶቱን ለማሰማት ሰልፉን ሲካሄድ የነበረው።

የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ፣ እጅግ የተጠላውና በሕዝብ ትግሉ ከገደል ጫፍ ላይ የደረሰው የህወሓት አገዛዝ ዕድሜውን ለማርዘም ሲል ዜጎችን በነፃ እርምጃ ለመግደል፣ ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ በጠራራ ፀሐይ እያፈሱ ለማሰር፣ ቤትና ንብረታቸውን ለመበርበርና

ለመዝረፍ፣ እንዲሁም ከእስር የተለቀቁ ጥቂት ወገኖቻችን ከሕዝባቸው ጋር እንዳይገናኙ ለመቆጣጠር የታወጀ አዋጅ መሆኑን ልብ ማለት ያስፈልጋል። በዚህ አዋጅ ህወሓት ጊዜ በመግዛት ያስተካከለ በመምሰል ተመልሶ በሕዝብ ላይ አሁን ካለው የከፋ ስቃይ ለማድረስ የታለመ አዋጅ ለመሆኑ ለመገንዘብ አያዳግትም።

በመጀመሪያ ደረጃ ህወሓት እራሱ ያወጣውን ሕግ ራሱ የሚሽር አጉራ-ዘለል ቡድን ነው። የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁም ከቶውንም አያስፈልግም ነበር። የህወሓት ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 93 እንደሚያመለክተው፣ "የሚኒስትሮች ምክር ቤትም ሆነ የሥራ አስፈጻሚው አካል አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ያስፈልጋል ብሎ ከወሰነ፣ ለፓርላማው አቅርቦ ማጽደቅ አለበት" ይላል። አያይዞም፣ "ፓርላማው በሥራ ላይ ከሆነ በ48 ሰዓት ውስጥ ዕረፍት ላይ ከሆነ ግን በ15 ቀናት ውስጥ ማጸደቅ አለበት" ብሎ ያብራራል። "ይህን ካላደረገ ግን የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ሕገ-ወጥ" መሆኑንም ያመለክታል። ስለዚህም ነው አሁን አገዛዙ በሥራ ላይ ያዋለውና ሕዝብን በጠራራ ፀሐይ የሚረሽንበት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ሕገ-ወጥ ነው የሚሆነው። ዓይኑን በጨው የታጠበው ህወሓት አዋጁን ህጋዊ ለማድረግ ሲዳክር የዓለም ሕዝብ ይታዘበኛል ሳይል እንደለመደው የፓርላማ ተብዬውን አባላት ድምፅ መጀመሪያ ያቀረበውን ቁጥር በመቀየር ከፍተኛ ቁጥር ሰጥቶ ፓርላማ ተብዬው አዋጁን አጽድቆታል ብሎናል። ህወሓት በተለያዩ ጊዜያት ባካሄዳቸው ምርጫ በተባሉት ቲያትሮች የሕዝብን ድምፅ እየሰረቀ አሸነፍኩ እንዳለ የሚታወቅ ቢሆንም የአሁኑን ለየት የሚያደርገው በአንድ አፍ ሁለት ምላስ መሆኑ ነው።

<u>የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ!</u>

"የነብርን ጅራት አይዙም ከያዙም አይለቁም" ነውና ከአባቶችህ የወረስከውን ጀግንነት ተላብሰህ፣ ከአስከፊ ሥርዓት ለመላቀቅ ትግልህን አጠንክረህ ቀጥል። ያሽመደመደኸውን የህወሓትን አገዛዝ ከሥሩ ነቅለህ እስካልጣልህ ድረስ፣ አንዳንድ እስረኞችን በመፍታቱ በሚያሳየው ድርጊት በዕውነት ለለውጥና ለተሃድሶ የተዘጋጀ አመራር መስሎህ ጭራሽ እንዳትዘናጋ አደራ እንላለን። ህወሓት ከስህተቱ ተምሮ የማይስተካከል፣ ሊስተካከል ይችላል ተብሎም የማይታሰብ የጠባብ ብሄርተኛ ቡድን ነው። በመሆኑም የቡድኑን ጥቅም እንጂ የአገርንና የሕዝብን ጥቅም የሚያስጠብቅ አይደለም። በብዙ ሺዎች ከሚቆጠሩት በቃሊቲና በአዋሽ እስር ቤቶች እየማቀቁ ካሉት ወገኖቻችን ጥቂቶችን መፍታቱ የትግልህ ውጤት ነው። ይህንንም የዓለም አቀፉን ማኅበረሰብ ለማታለል ይጠቀምበታል። በሌላ በኩል እስረኛ ፈታሁ እያለ በየቀኑ ጨለማን ተገን በማድረግ ሌሎች ወገኖቻችንን እያፈነ በመውሰድ ብዙዎችን ወደ እስር ቤት መወርወሩን እንዳላቋረጠም ልብ ይሏል።

በአገራችን በኢትዮጵያ ምድር በሚገኙ ሥፍር ቁጥር የሌላቸው እስር ቤቶች ውስጥ በከፍተኛ ቁጥር ከሚገመተው የነፃነት ታጋይ እስረኛ ውስጥ ብዙሃኑ ወጣትና አዛውንት መሆናቸውን በእስር ሲሰቃዩ ቆይተው የወጡት ወገኖቻችን የመሰከሩት ሃቅ ነው።

አንድ ልንገነዘበው የሚገባ ጉዳይ ቀደም ብሎ ታወጆ የነበረው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ተነሳ በተባለበት ጊዜ እንኳን በአንዳንድ አካባቢዎች ወታደራዊ ወከባው እንዳልተቋረጠ ነው። ስለዚህ አዲሱ አዋጅ እስከሁን ከነበረው መከራና ወታደራዊ ወከባ፣ ግድያና እስራት የተለየ ምንም የሚያመጣው መልካም ነገር አይኖርም። እንዲያውም የባሰ የሚያደርገው፣ ህወሓት የሚለፍፈውን ሃቅ ያልተላበሰውን የሰላም ለውጥ ወይም ተሃድሶ ተስፋ በማድረግ ተዘናግተን የትግል ክንዳችንን ካጠፍን ነው።

ስለዚህ ዜጎች ሁሉ በመተባበር ጠንክረን መታገል አማራጭ የሌለው ግዴታችን ነው። **<u>ሕልውናችንና መብታችን የሚከበረው ህወሓት ከሥልጣን ተወግዶ በአገራችን ሰላምና ዴሞክራሲ ሲሰፍን ብቻ ነው።</u>**

በመጨረሻም፣ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (አንድነት) በጠባቧ እስር ቤት ለዓመታት ሲሰቃዩ የነበሩ ወገኖቻችን፣ የመከራ ቋት ከሚገፋው ሕዝባቸው ጋር ለመገናኘት በመብቃታቸው የተሰማው ደስታ እጅግ በጣም ከፍተኛ ነው። አሁንም በቀጣይነት ህወሓት የሚፈጽመው አፈና፣ ግፍና መከራ የኢትዮጵያውያን ሁሉ ስቃይና መከራ ነውና መፍትሄ ለማምጣት ለሚደረገው ተጋድሎ ኢሕአፓ (አንድነት) ምንጊዜም ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጎን እንደሚቆም ያረጋግጣል።

የኢትዮጵያ ሉዓላዊነት በሕዝቦቿ አንድነት ይከበራል!

**P.O.Box 91384** **Phone: 202- 241 2078**
**Los Angeles, CA 90009** **eprp_united@eprp-ihapa.com**